**ጥቅምት  15 2016**

የሰሜን አሜሪካ የአማራ ፌዴሬሽን (ፋና) አዲስ አመራር ለመምረጥ የተሳካና ግልፅ የሆነ ምርጫ ጥቅምት 14 2016 ዓ.ም(October 25 ቀን 2023)  አካሂዷል።

በሰሜን አሜሪካ ለሚገኙ ለ17 የአማራ ድርጅቶች ጥላ የሆነው ፋና መተዳደሪያ ደንቡን መሰረት በማድረግ የሥራ ዘመናቸውን ባጠናቀቁ የፌደሬሽኑን መሪዎች በአዲስ ተመራጮች ለመተካት ባካሄደው ግልፅ ምርጫ የተመረጡ አዲስ አመራሮችን በደስታ ለመቀበል ይወዳል።

በዚህ ግልፅ እና የተሳካ ምርጫ መሰረት የተመረጡ የፌደሬሽናችን ተተኪ መሪዎች

1. የፋና ፕሬዝዳንት፡ አቶ የዚህዓለም መስፍን (የሚኒሶታ የአማራ ቅርስ ማህበር ተወካይ)
2. የፋና ምክትል ፕሬዝዳንት፡ ወ/ት ቤተልሄም አየለ (የሎስ አንጀለስ የአማራ ማህበር ተወካይ)
3. የፋና ጸሐፊ፡ ወ/ሮ ራሄል አባተ (የኔቫዳ የአማራ ማህበር ተወካይ)
4. ፋና ገንዘብ ያዥ፡ አቶ አንተነህ ይማም (የዳላስ አማራ ህዝብ ሲቪክ ድርጅት ተወካይ)
5. የፋና የህዝብ ግንኙነት፡ አቶ ላዕከ ምስክር (የአማራ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ)
6. የፋና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር፡ አቶ መስፍን ዘመድኩን (የኔቫዳ የአማራ ማህበር ተወካይ)
7. የፋና ማህበረሰብ ትስስር ዳይሬክተር፡ አቶ ቢኒያም ቅጣው (የሎስ አንጀለስ የአማራ ማህበር ተወካይ)  ሲሆኑ።

በአንፃሩ ኃላፊነታቸውን ለአዲሶቹ ተመራጮች እያስተላለፉ ያሉት ተሰናባች  የፋና አመራሮች  ላለፉት ሁለት ዓመታት ፋናን ለአማራ ፋኖ ንቅናቄ የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለገለ ጠንካራ የማኅበራት ኅብረት ወይንም ፌደሬሽን በመገንባታቸው  ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። ፋና በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በተመለከተ ህዝብን የማንቃት፤ የቅስቀሳ እና ተቃውሞዎች በሰፊው እንዲሰራ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ በማሰባሰብ ከልዩ ልዩ ቦታዎች ለተፈናቀሉ አማራ ወገኖቻችን ሰብአዊ እርዳታ አድርገዋል።

የቀድሞ የፋና መሪዎች

1. የፋና ፕሬዝዳንት፡ አቶ ቴዎድሮስ ትርፌ (የአሜሪካ የአማራ ማህበር ተወካይ)
2. የፋና የህዝብ ግንኙነት፡ ወ/ት ቤተልሄም አየለ (የሎስ አንጀለስ የአማራ ማህበር ተወካይ)
3. የፋና ጸሐፊ፡ አቶ መስፍን ዘመድኩን (የኔቫዳ የአማራ ማህበር ተወካይ)
4. ፋና ገንዘብ ያዥ፡ አቶ ግዛቸው በላይ (የካሊፎርኒያ (ሳን ዲዬጎ) የአማራ ማህበር ተወካይ)
5. የፋና ማህበረሰብ ትስስር ዳይሬክተር፡ አቶ ሙሉጌታ መኮንን (የአማራ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ)

   ናቸው።

በተጨማሪም ፋና ይህን ግልፅ እና  ፍትሃዊ ምርጫ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱትን የምርጫ ግብረ ኃይሉን አባላት ማመስገን ይወዳል።  የምርጫ ግብረ ኃይል አባላት የሚከተሉት ናቸው -

1. ወ/ሮ ሳራ ሺመልስ፡ (የዳላስ አማራ ህዝብ ሲቪክ ድርጅት ተወካይ)
2. አቶ ሙሉጌታ መኮንን (የአማራ ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ)
3. አቶ ምስጋናው አበበ (የጆርጂያ የአማራ ማህበር ተወካይ)
4. አቶ ተስፋየ ንዋይ (የሚኒሶታ የአማራ ቅርስ ማህበር ተወካይ)

ተሰናባቹ የፋና ፕሬዘዳንት አቶ ቴዎድሮስ ትርፌ  አክለውም "ፋና ጠንካራ የአማራ ተቋማትን የመገንባት ጉዞውን ለማስቀጠል ጠንካራ እና የተለያየ ዓይነት አባላት ያሉትን አዲስ አመራር ተተክተው በማየቴ በግሌ ክብር ይሰማኛል ብለዋል፡፡ ተሰናባቾቹ የፋና አመራሮች በሽግግሩ ወቅት አዲሱን አመራር ለመደገፍ ቁርጠኛ  እና የፋና መጻኢ ስኬት ደስታቸው እንደሆነ ገልጸዋል። አዲስ የተመረጡት የስራ

አስፈጻሚዎችም በዚህ ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ወቅት የተጣለባቸውን ሃላፊነት እና አደራ በትጋት እና በታማኝነት ለመወጣት ቃል ገብተዋል።

የአማራ ህዝብ በአቢይ አህመድ አሊ እና በኦሮሙማ ርዕዮተ ዓለም ወታደራዊ አፈና ውስጥ ሆኖ ዘር አጥፊ ጦርነትን በመጋፈጥ ላይ ይገኛል። በአዲሱ አመራር ስር ፋና ከአባል ድርጅቶች፣ አጋሮችና ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በአማራ ላይ በአብይ አህመድ መሪነት የተከፈተውን ይህን የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለማስቆም እና ወንጀለኞቹን ለፍርድ ለማቅረብ ይተባበራል። ተሰናባቹ አመራር ፋናን እና ሁሉንም አባል ድርጅቶች አጠናክረን ለመቀጠል ለመጪው የፋና አመራር ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል።

ከንዳችን መዳኛችን!!!

ቴዎድሮስ ትርፌ

የቀድሞ የፋና ፕሬዚደንት